ስትራቴጂ በታዎቹ የማያቋርጡ የገቢ ምንጮቹና የስራ ዕድል ፈጣሪዎቹ ናቸው ::

እንግዲህ አግዚአብሔር ያሳይሽ የአሜሪካ ህዝብ ሶስት መቶ ሚሊዮን ነው በቴሌቪዥን እንዳየሺው የሀገራችን ህፃናቶች በጣም ያሳዝናሉ ብዙ ሰው ሲያያቸው አንደኛው እንጀቱ ይላወሳል እናም አሜሪካ ውስጥ ደግሞ ከ 95 በመቶ በላይ ቴሌቪዥን አምላኪ ነው ::

ጊዜ ካገኘ የሚያገኘው የአሜሪካ ህዝብ ደግሞ ለአንደዚህ ዓይነት አሳዛኝ ነገር ሲተባበር ደስ ይለዋል፤ እንግዲህ በጣም በትንሹ 500 ሺው ህዝብ እንኳን ቢረዳ በወር ወደ 12 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ያገኛሉ ማለት ነው ፤ አስቢው በኛ ስም የተለመነም ነውና ለረሀቡ ብቻ ብለው በየወሩ አንድ ሚሊዮኑን እንኳን ቢሰጡን ረሃብ ከኛ አገር ደህና ክረሙ በቃ ሁለተኛ እንገናኝም ብሎ ይሰናበተን ነበር ፤ ይህ ግን ሆኖም አያውቅም ወደ ፊትም አይሆንም ፤ ረሃቡን እስከመጨረሻው ሁስተኛ እንደይመጣ ድራሹን የምናጠፋውም የምናመጣውም እራሳችን ነን በኛ ስም ተለምኖ የተገኘው ብር ለኛው ይመጣል ብሎ ማሰብ ማለት ለዚህ መቸም ተረት አያስፈልገውም ፤ ገንዘቡን ሲበሉት ደግሞ እንዲህ በድፍረት ማናባቱ ይናገሩናል ብለው እንዳይመስልሽ ብዙ ብልሃት አላቸው፤ ለማስታወቂያ ለመጓጓዣ ለፅህፈት ቤት ለኮምፒዩተሮች ... ወዘተ ብለው ጉምድምድ አድርገው ያነክቱታል አልሻለሁ

ለመሆኑ ያገራችን መንግስት ረሀባችንን አስቁማችኹ ለማታስቆሙት በቃን አትለምኑብን ጠቀማችሁ ለማትጠቅሙን በየሄድንበት አንገታችንን አታስደፉን ብለው ማስቆም ለምን አልሞከሩም ?

ምነው ልጄ መንግስታችን የናንተን እርዳታ አንፈልግም ካለማ ስልጣኔንም አብራችሁ ተረከቡኝና ካለእናንተ እርዳታ አገሪቷን ለሚመራ ስጡት ነው የሚለው ምክንያቱ ብዙዎቹ የታዳጊ አገሮች የኛን አገር ጨምረው መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ካልተረዳ ተሽመድምደው ቁጭ ነው የሚሉትና በዕርግጥ የምትይው ይገባኛል

ታዲያ እንዳይለምኑበን ለማስቆም ምን ማድረግ እንችላለን?

ብዙ ነገር ማድረግ ይቻላል ከዛፍ መትከል እስከ ፋብሪካ መቋቋም ሳይታከቱ ለራስም ለሀገር ክብርም ሲሉ መስራት ፤ መጣር ፤ መጋር ያስፈልጋል እንዳለችው መለፋቱ መደከሙ መች ቀረና ጠብ እልል ብሎ እንጂ የዓለም ህዝብ እንደሚያውቀው አውሮፓና አሜሪካ ውስጥ ብዙ ድርጅቶች በእርዳታ ማስተባበሪያ ስም ሀብት አካብተውብናል :: የጠላንም እንቋሾናል ፤ የወደደንም ምድር ገነት ኢትዮጵያ ብሎናል

አድሜ ለመንግስቱ ኅይለ ማርያም ህዝባችንን አስገድዶ አብዮት አደባባይ ሰብስቦ " የአሜሪካኖችንም ሆነ የተከታዮቻቸውን ደም እናፈስዋለን " ብሎ ሲራገም መመሪያችን ሶሻሊዝም ብሎ ሲፎክር ህዝቡም ሳይወድ በግዱ ሲያጨበጭብለት የተቀረጸውን የአሜሪካ ባለስልጣናት አይተውት ቂም በመያዝ ሶሻሊዝምን ለማጥላላትና ሶሻሊዝም መጨረሻው ህዝብን ማስራብ ነው ብሎ የአሜሪካም ህዝብ እንዲቀበለው የተራቡ የአገራችንን ህፃናት ፍቶ ግራፍ ልክ

ከማንም ጋር በየቀኑ ረዘም ላለ ሰዓት እንኳን ስለማያገናኝ ይህ ነው ስራ ብላ መርጣዋለች ::

የላስቬጋስን ታክሲ በዓለም ላይ ካሉ ታክሲዎች ሁሉ ለየት የሚያደገው ሰማይ ቢወጣና ቢወርድ የግል ታክሲ እስመፈቀዱ ነው።

ወደ 6000 ሺ. ታክሲዎች ከ 15 የማይበልጡ የታክሲ ካምፓኒዎች ሲኖሩት ታክሲዎቹ ለስራ ወጥተው እስከሚገቡ የሚቆጣጠሩላቸው የታጠቁ ዘበኞች ሲኖሯቸው ካምፓኒው የታክሲውን ዕዳት ጥንካሬ እና ሹፌሮች ገንዘብ ወደ ኪሳቸው ሳይወስዱ በትክክል ወደ ካምፓኒው ማስገባታቸው ለሚቆጣጠሩላቸው ደሞዝ የሚከፈለው ከሹፌሮቹ ድርሻ ላይ እየተቆረጠ መሆኑን አውቃ እሜን ብላ ተቀብላ ሰመጀመር ተፍ ተፍ እያለች ነው። በተለይ መኪና መንዳት ባጭር ግዜ መልመዷ ታክሲም ሰመንዳት የባሰ ጉጉት አሳድሮባታል።

# ምዕራፍ አስራ ዐራት

ትርሲት ይህን ሁሉ ከተገነዘበች በኋላ ሁሉ ታክሲ ወይም ሞት ብላ ላስቬጋስን አብጠርጥራ ማወቋን በፈተና አረጋግጣ በየቀኑ ከ 60 እስከ 70 ሺ. ቱሪስት በሚንጋጋባት ላስቬጋስ መሃከል ታክሲውን ይዛ አቤት ጋሽዬ እመት እትዬ የት ላድርሳችሁ ማለቱን ተያይዛዋለች ::

ቀን ቀን ትምህርቷን ማታማታ ታክሲዋን እያሽከረከረች ለሚያያት ኢትዮጵያዊ ኩራት ሆናለች ::



ከሰው ለምን እንደምትርቅ እልፍ እልፍ ሁኔታዋን ያዩ ሲጠይቋት ጊዜ ስለሌለኝ ነው የሚል እጥር ምጥን ያለ መልስ ብትሰጥም እንኳን ኢትዮጵያኖች የሌላ እገር ዜጎችም ትርሲትን ለማነጋገር የማያደርጉት ጥረት የለም እሷ ግን ቆሞም ሆነ ተቀምጦ ለማውራት ጊዜ የሌላት መሆኗን ለማሳየት የማትጠቀመው ዘዴ የላትም ::

አንዳንድ ጊዜ የታክሲው ስራ ቀዝቀዝ ሲል ወረፋ ሲጠብቅ መገተር ስለሚኖር ከኋላ የተሰለፉት በተለይ ወጣት ወንዶች በሩን እንኳኩተው ሲሞክሩ ሰልኳን ብድግ አድርጋ የተደወለላት በማስመሰል በጣቶቿ ከንፈሯን በመደብደብና ጠቋሚ ጣቷን ወደ ስልኳ በማመልከት መስኮቷን ትዘጋባቸዋለች ::

ለምን እንደዚህ እንደምትሆን ደግማ ደጋግማ እራሷን ትሰጠይቅ ኽ ኽ ኽ እጉል ከሰው መላመድ ኋላ ጣጣው መከራ ነው መልሷ ፡ ላስቬጋስ ውስጥ በወር ቢያንስ ሁለት ጊዜ ከ 20 ሺ. እስከ 200 ሺ. የሚገመት ህዝብ ከኮንቬንሽን ወይም ለመገበያየት የሚመጣ ሲሆን በተለይ እየር ማረፊያ የታክሲ እጥረት ከገጠመው የታክሲ ካምፓኒው ዲስፓቸሮች የለማቋረጥ እየጮሁ ስለሚያሯሩጧቸው የነሱን ቃል ሳያከበር ቆሞ የተገኘ ሹፌር እስከ ስራ መባረርም ስለሚደርስበት ቃላቸውን እየሰማ ወደ ተፈለገበት የማይከንፍ የለም ትርሲትም የነሱን ቃል ለማክበር ሰትከንፍ በሰዓት 35 ኪ.ሜ መንዳት ያለበትን እካባቢ 45ኪ.ሜ በሰዓት ስትንዳ ከየት መጣ ከየት ሳይታወቅ ከትርሲት ኋላ ሆኖ ልክ እንደ ኋይለኛ መብረቅ ለማያዊ ቀይ ቢጫ ድብልቅልቅ ያለ መብራት አብለጭልጮ ከእሳት እደጋ ወይም

የተባረረ ሲሆን የታክስ ኪምፓኒ ባለስልጣን ደግሞ የፖሊስ ልምዱ ከኛ ህግ ውጪ በመወራጨት የራሳቸው የሆነ ታክሲ እንዲኖራችው ፈቃድ ለማግኘት የሚሞክሩበትን ታክስ ነጂዎች ልክ ያስገቡልናል ብለው ከሚቀጥሯቸው አንዱ አድርጎ ነው የተቀጠረው ::

አድሜው ወደ 36 የሚጠጋ ሲሆን ሦስት ጊዜ አግብቶ ፈቷል ከሦስቱም ሚስቶች የተፋታበት ምክንያት በትዳር ላይ በመማገጥ ነው :: አሁን ግን ታየሁ አልታየሁ ብሎም ስለማይጨነቅ ካገኘው ጋር መዳራት የዘውትር ተግባሩ ሆኗል ::

ከትርሲት እንደተለየ ብዙም ሳይቆይ ታክሲ ወደምትነዳበት ካምፓኒ በመሄድ መዝገብ ቤት ገብቶ ትርሲት ስለተባለች ታክሲ ነጂ የደረሰን ጥቆማ ስላለን ብሎ ፋይሏን አስመጥቶ ማንነቷን አያገላበጠ ምንጥር አድማን ከተገነዘበ በኋላ መዝገቡን መልሶ የታክሲ ካምፓኒዎች አየከፈሉት ነገር ግን የራሱን ስራ ወደሚያከናውንበት ስራው ተሰማራ::

በተለይ ትንሽ ጠጣ ያደረጉ ትርሲት የምትነዳው ታክሲ ውስጥ ሲገቡ ፊቷ ልውጥውጥ ብስጭትጭት ትላለች ፤ አብዛኛውን ጊዜ ከመቶ ዘጠናው እጅ አገርሽ የት ነው የማይቀር ጥያቄ ስለሆነ ሆኖም ግን ለሁሉም መልሷ ኢትዮጵያዊ ሲሆን ከ 100 አምስት እጅ የሚሆነው ህ እንዴት ታድለሻል ! ኢትዮጵያ እኮ የመጀመሪያው የሰው ዘር የኖረባት የነሉሲ አገር ኢትዮጵያ የታሪክ ሀብታም የኢኮኖሚ ደሀ ሲሏት በመጠኑ ፈገግ ትልና የተቀሩት ደግሞ ዋው አንኳን ወደዚህ መጣሽ መቸስ በጣም ትልቅ ለውጥ ነው አይደል ፤ ለመሆኑ ከአገርሽ ስትመጪ ክብደሽስ ስንት ነበር ? ኢትዮጵያ እኮ



ልጆቹን የማስፈራራበት አገር ነች ፤ ልጆቹ የስራሁላቸውን ምግብ አለበላም ሲሉኝ ወደ ኢትዮጵያ ነው የምልካችሁ ስላቸው ድንግጥግጣቸው ወጥቶ አሺ ማሚ ይቅርታ ነው የሚሉኝ ::

ክንዷን እየነኩ ህ እዚህ ብዙ ምግብ ስላለ ጡንቻ አወጣሽ ? የዘወትር ቋንቋቸው ስለሆነ ልትላመደው ያልቻለችው ቃለ ምልልስ ሆኖባታል ::

ባስ ሲልባት ለመሆኑ እናንተ ማን ሆናችሁ ነው ? የተከበረች የነጻነት አርማ የሆነችን አገር የምታጥላሉት አሜሪካኖች ከሆኑ እንግሊዝ የአግሩ መጥረጊያ አድርጓችሁ አልነበረም ስፓኒሾቹን ስፔንን ጠይቁ ተርበው የነበረበትን ዓመተ ምህረት አየጠቀሰች አሱንም ብታስታውሱት ይሻላቹኋል ስትላቸው ትንሽ ደንገጥ ብለው አደብ ይገዛሉ ::

መቸስ የላስቬጋስ ታክሲ የማያገኘው የዘር ዓይነት የለም ስፓኒሹ ፤ ጥቁሩ ፤ ነጩ ፤ ህንዱ ብቻ ምኑ ቅጡ የሚገርመው ለሁሉም የምትለው አላት ::

ሜክሲኮውን ስታገኝ አያችሁ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ኢትዮጵያውያኖች ሜክሲኮን በጣም እንወዳለን ምክንያቱም ጣሊያን በመርዝ ጭስ ይጨርሰን የነበረ ጊዜ ሜክሲኮ የተቃውሞ ድምጹን በማሰማቱ ለዚያ ውለታው አንድን ስፈር ሜክሲኮ አደባባይ ብለን ጠርተነዋል ብላ ታስደስታቸዋለች የአሜሪካን ጥቁሮች ሲያጋጥሟት ደግሞ እኛ ኢትዮጵያኖች ለእናንተ የተለየ ክብር አለን እናንተ ታግላችሁ ነፃ ባትወጡ ኖሮ እኛም ባሪያ ሆነን ነበር የምንመጣው እኛ ኢትዮጵያኖችም ለነጻነታችን ከጣሊያን ጋር ስንፋለም ጣሊያን ከኛ የተሻለ

አክስንቱ የሌላ አገር ዜጋ መሆኑ ያስታወቀበትን የቅጣት ትኬት በመፃፍ የታወቁ ሆኖ ሳለ ትርሲት አይን ያወጣ ጥፋት እጥፍታ ዛሬ ታልፈሻል መባሏ ሌላ ግርማ ሌላ መለኮት እንዳይፈጠርባት ሁል ጊዜ እንደተርበተበተች ነው ::

ማንኛውም የሰው ፍጡር ጤነኛ እስከሆነ ድረስ በህይወት ዘመኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ ያፈቅራል ወይም ይፈቀራል ፤ በዓለም ላይ ያሉ ህዝቦችን ስለ መፈቀርና ማፍቀር አንድ የሚያደርጋቸው ብዙዎች ቢሆኑም ጥቂቶች አስቀያሚ አካሄዶች ግን ወደድኩሽ (ህ ) ባዩ እምቢ ከተባለ እራሱን ሰላም ነስቶ አጉል ከመለፍለፍ ብዛት የሰውን አመለካከትና ፍላጎት ይቀይር ይመስል አኝኝኝ ሲል ይከርማል ፤ ሞክሮ ሞካክሮ ካልተሳካለት በተንኮልና በመሰሪነት ስበቀል ይነሳሳል።

በዚህ ዙሪያ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ሰላሳት እንደመፍትሔ አድርጋ ለጊዜው የያዘችው"ስርሳይስድበእንጭጭነቱ"የሚለውን ነው።

ጄምስ ደግሞ ደጋግሞ የተለያዩ ግብዣዎችን እቅርቦላት እንደማትችል መንገር ብቻ ሳይሆን እጮኛ እንዳላት ብትነግረውም እንዲያውም ለምን በሚስጥር አናደርገውም " ዋት ሀፐን ኢን ቬጋስ ስተይስ ኢን ቬጋስ " ሲባል አልሰማሽም? ብቻ ምኑ ቅጡ ሊያሳምናት ቃላት መደርደር ብቻ ሳይሆን እሷን የሚግባቧትን ለማገኘት ያልሞከረው መንገድ የለም ::

ትርሲትን ለማግባባት ይጠቅሙኛል ያላቸውን ኢትዮጵያኖችን ለማገኘት ያመጣው ዋና ዋና መመዘኛዎቹ ታክሲ ነጂ የሆነን በሚሰራበት የታክሲ ካምፓኒ ውስጥ ችግር



ያለበትን ማጠመድ ሲሆን ዕቅዱን ለማሳካትም በየታክሲ ካምፓኒው እየዞረ ችግር ፈጣሪ ታክሲ ነጂዎች እንዳሉ ሲጠያይቅ ቬጋስ ዌስተርን የተባለውን ካምፓኒ ውስጥ ተፈሪ የተባለ ኃይለኛ የቁማር ሱስ ስላለበት ሲሰራ የዋለውን ገንዘብ ለካምፓኒው በማስረከብ ፋንታ በቁማር እየተበላ እካምፓኒው በር ላይ እየቆመ አበድሩኝ ዕቃ ግዙኝ እያለ ሌሎቹን ሹፌሮች ዘወትር ሰላም ይነሳል ::

ጄምስ ጊዜ ሳያጠፋ ተፈሪን እቢሮው በማስጠራት ለምን እንደመጣህ ታውቀዋለህ ? እካምፓኒህ በር ላይ እየቆምክ የምትሰራውን ስለምታውቀው መድገም አልፈልግም ይህን ድርጊትህን የማታቆም ከሆነ ላስቬጋስ ማንኛውም በታ እንዳትቀጠር ሽሪፍ ካርድህን ትነጠቃለህ ፤

እሺ ሁለተኛ አይለምደኝም ብሎ እጅ ሲነሳ

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያዊ ነህ ?

እዎ ነኝ

ቬጋስ ዌስተርን የምትሰራ ትርሲት የምትባለውን ታውቃለህ?

አ እንጀሊናን አዎ አውቃታለሁ በጣም ቆንጆ ስለሆነችና ችግር ደራሽ ስለሆነች እኔ ነኝ አንጀሊና ብዬ ያወጣሁላት

ቆንጆናዋንን እንኳን ልክ ነህ ለችግር መድረሷን ግን አላውቅም አረረ ለችግርማ ትደርሳለች በጣም አዛኝ ነች እኔ እራሴ ነው ያየኋት ፤ ባለፈው ወር ስሰራ የዋልኩትን ስቆምር ተበላሁና የሚያበድረኝ ሳጣ የጎደለብኝን ለመሙላት ዳውንታውን ያለው ፐላዝማ ሴንተር ባቶማ ዩኤስ ሄጄ ደሜን

ወ/ሮ ሱዛን የስልሳ ዓመት ጠንካራ ሴት ሲሆኑ ገንዘብ ችግራቸው ሳይሆን ቤት መቀመጥ በጣም ስለማይወዱና ከሰው መነጋገር ስለሚፈልጉ እሳቸውም ታክሲ ነጂ ናቸው ። እረፍት እንኳን የሚያርፉት ጠበቃዋና ፖሊሱ ልጆቻቸው ሊጠይቋቸው በየሳምንቱ ሲመጡ ብቻ ነው ።

ስለ ትርሲት ውበትና ቁንጅና ብቻ ሳይሆን ስለስነስርዓቷ ባገኙት አጋጣሚ ማውራት ደስ ይላቸዋል ።

ከስራዋ የመታገዷ ሁኔታ በጣም ሲከነክናቸው ከርሞ ትርሲት ጋር ስመደወል የቤታቸውን አድራሻ ነግረዋት በመሄድ ስለሁኔታው እንባዋን እዘያራች ጄምስ የተባለ የታክሲ ተቆጣጣሪ የሱን ፍላጎት ላሟላ ባለመቻሌ ጥፋቶችን እየፈበረከ እኔ ያደረኳቸው በማስመሰል ተከሰኝል እያለ ከዚህ ችግር ልትወጪ የምትችይው ደግሞ ከኔ ጋር ከተስማማሽ ብቻ ነው የሚል እዝማሚያ እያሳየ መጠቀሚያ ሊያደርገኝ ነው በማለት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍርጥርጥ አድርጋ ስትነግራቸው በጣም በማዘን ምነው የኔ ቆንጆ እስከ ዛሬ ብትነግሪኝ ኖሮ መፍትሔ እናጣም ነበር ፤ ለማንኛውም እይዞሽ ብለው አጽናኗት ።

ወ/ሮ ሱዛን ለልጆቻቸው ነግረው ትርሲትን ካስተዋወቋት በኋላ በተመከረችው መሰረት ወደ ጄምስ ቢሮ በመሄድ " በቃ ወደ ስራዬ እንድመለስ ተባበረኝ እንጻስብበት ግን የተወሰነ ጊዜ ስጠኝ ስትለው ገና ከቢሮው ሳትወጣ ወደ መስሪያ ቤቷ ደውሎ የትርሲት ሁኔታ መፍትሔ ስለተገኘለት በመጣች ሰዓት ስራዋን መቀጠል ትችላለች ብሎላት ወደ ስራዋ እየበረረች ሄደች ።



ተፈሪ በየሄደችበት በተለይ ኢትዮጵያውያኖች ባገኙት አጋጣሚ ያላቸውን ቅሬታና በተለይ በትርሲት ላይ የሚያስወራውን አሉባልታ ስላልወደዱለት ማፈናፈኛም ስላጣ ብዙዎቹን ይቅርታ ጠይቆ ወደ ካምፓኒው ጽ/ቤት በመጠጋት የነጻ ጉልበት እያበረከተ ሲወነብዱ ከርመው የማታ ማታ ሃይማኖተኛ ሆነው ካለኔ የሃይማኖት እስተማሪ የለም ያዙኝ ልቀቁኝ እንደሚሉት ዓይነቶች የስራውን ስህተት ባገኘው አጋጣሚ እያወራ በህይወቱ ላይ ትልቅ ለውጥ ማምጣቱን እሱም መስካሪ ሆኗል ።

ወ/ሮ አምሳለ የእትዮጵያውያን ሬስቶራንት ለመክፈት ኢትዮጵያዊ በብዛት ወደሚኖርትበት ዋሽንግተን ዲሲ እካባቢ ጠቅልላ ከሄደች ጀምሮ ትርሲት የአፓርታማ ብቸኝነት ኑሮን ኑሮ ብላ ተያይዛዋለች ።

በተለይ ጄምስ ከስራ ቀን የታክሲ እውቶሪቲ የስጠውን በትልቁ ፖሊስ የሚል በዓይን ማየት በሚያስቸገር ሁኔታ የታክሲ አውቶሪቲ ተብሎ የተጻፈበትን መኪና በረፍት ቀኑ ደግሞ የግል መኪናውን እየያዘ ትርሲት የምትኖርበት አፓርታማ በየቀኑ እየመጣ ትርሲትን በወጣች በገባች ቁጥር ሰላምታ ይሁን ማስፈራራት ማወቅ በሚያስቸግር ሁኔታ ይቅለስለስባታል ።

ይህ ሁኔታው በጣም ስላሳሰባት ለወ/ሮ ሱዛን ልጅ ነግራው እሱ ደግሞ ከስራ ባልደረቦቹ ጋር በመነጋገር እስፈላጊውን ባለሙያ መድበውበት የጄምስን እያንዳንዷን እርምጃ እየቀረፀ ነው ።

ትተው ለመቀየር እኔ ነኝ ቀድሜ የጠየኩት እዚች ክፍል ውስጥ ካለኔ የሚተኛ የለም እያሉ ሲጨቃጨቀ እየሁ፤ በጣም ገርሞኝ ጓደኛዬን ለምንድ ነው እንደዚህ የሚሆኑት ክፍሎቹ ሁሉም አንድ ዓይነት ይመስሉኛል ብዬ ጠየኩት በጣም ተገርሞ ለምን መሰለህ እዚያች አሁን የሚጣሉባት ክፍል ውስጥ ይኖር የነበረ ልጅ DV ወጥቶለት ወደ አሜሪካን ስለሄደ እድለኛ ክፍል ስለሆነች እንዲቀናቸው ብለው ነው ሲለኝ እኔም ግርም ብሎኝ የህዘን ሳቄን ሳቅሁ እልሻለሁ ፡፡

የውጭውን ኑሮ እኔ አንብቤ ከማገኘው የበለጠ አንቺ ስለምትነግሪኝ በኔ በኩል ለዘመናዊ ባርነት ምን አገሬን ጥሎ ያስኬደኛል ነው የምለው ፡፡

አንዳንድ እናቶች እንኳን አሜሪካን ደርሰው ከተመለሱ በኋላ ዘመዶቻቸው ድጋሚ ግብዣ ሲያቀርቡላቸው ስለ ሃሳብህ እመሰግናለሁ ትኬት የምትገዛበትን ላክልኝ ወይም እኔ እዚሁ አገሬ ብቸገር ይሻለኛል እንደዚያ ሌት ተቀን እንቅልፍ አጥተህ ያገኘኸውን ገንዘብ በፍፁም እልፈግም ምንም ነገር እንዳትልክልኝ የሚሉና አልፎ አልፎ ደግሞ ገና ከውጭ ስልክ ሲደወልላቸው " በል የኔ ልጅ የናንተ እገር ስልክ በድንገት ነው የሚቋረጠውና ወረቅትም እስክሪቢቶም ስላዘጋጀሁ ገንዘቡን የላክበትን ቁጥር ነገረኝ የሚሉም እሉ ፡፡ በአጠቃላይ በተለይ እሁን አሁን በአገራችን ብዙ የሚያስገርም ነገር እየታየ ነው ፤ እዚህ የሚኖረው ህዝባችንን በሙሉ ዲቪ ወጣልህ ቢባል " ባፍንጫዬ ይውጣ " የሚለው ስንቱ እንደሚሆን ስታቲስቲክስ ስሰራ ጊዜዬንም አላጠፋ እውጭ ያለው ደግሞ እንችም እንደነገርሺኝ አንዳንዱ ወደ እገሩ እየተመለሰ ነው ብዙዎቹ



ሁል ጊዜ ሻንጣ እንደገዙ ሻንጣቸው ለብዙ ጊዜ ባዶውን ሲቀመጥ ብቻ ወይ እዚያው አሜሪካን ቀርተው እልቀሩ ወይ ቆርጠው እገራቸው አልገቡ እንዲያው በምኞት እንደባዘኑ ይኖራሉ ምስኪኖች

የሚገርሙት ግን አሜሪካን አገር ቤት ሲገዙ የተበደሩት ወለዱ እያናጠረባቸው ሌላ ቤት እገራቸው ውስጥ በማሰራት እዚያም እዚህም እያሉ ሁለት ፊት ኑሮ የሚኖሩት ናቸው በእርግጥ ለነዚህ ታፔላ መስጠት ይከብዳል ምክንያቱም እስር ሰው ጥቅማቸው ምንድ ነው ብለሺ ብትጠይቂ ሀያ ዓይነት መልስ ነው የምታገኚው ፡፡

ይህንን ሀሳብ ላነሳው የፈለኩበት ዋናው ምክንያት ባለፈው ጊዜ ስንነጋገር እንች ከመምጣትሽ በፊት አሜሪካን እገር ቤት ገዝቼ ብመጣ ጥሩ ነው ያልሽኝ ሁኔታ ስላሳሰበኝ ነው፤ ትርፉ ስለማገኘት ከሆነ የቤትም ሆን የመሬት ዋጋ በእገራችን ታሪክ ውስጥ ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ ታይቶ እይታወቅም አሜሪካን ግን ያው እያየሽው ስለሆነ " ምጥ ለናቷ" ዓይነት ነው የሚኖንብኝ ስለዚህ ቁርጥ አድርገሽ ሃሳባቸንን ሳንበታትን መኖር እንድንችል ወደ አገርሽ የመመለሱን ሁኔታ እስብቢበት

በተወያየነው መሠረት ዘወትር እሁድ ገብረብሩክን እየተመላለስኩ ስጠይቀው ከርሜ ባለፈው እሁድ ትርሲትና መክብብ የተባሉ ምናቸውንም እልፈልግም ብሎ መልዕክት ልኩብኝ እኔም የሰራው ስህተት ፀፀቱ ዕረፍት እንደነሳው ገብቶኝ ላለመሄድ ወሰኛለሁ እሱን ብቻ ሳይሆን ፖሊሶችን እና ወንጀሉን የሚያውቁትን ሁሉ የገረማቸው የአንቺ ፍርድቤት

አንደምን አደሩ የተከበሩ ዳኛ

ለመሆኑ ባለቤትዎ እንዴት ናት ? መቼስ በጣም ነው የማዝነው

አግዚአብሔር ይመስገን ሂወቷ ተርፎልኛል

በጣም ጥሩ

ወ/ሪት ትርሲት አምባዬና አቶ ዶን ሽሬዝ ብለው ሲጠሩ

አቶ ዶን ቀርበናል የተከበሩ ዳኛ አንዳሉ

ወ/ሪት ትርሲት ለተከሰስሽባቸው ወንጀሎች ምን ታሲቢያለሽ?

እኔ ጥፋተኛ አይደለሁም ስምንድን ነው ? አስጥፋቴ አንዲህ የምታስቃዩኝ ብላ የሰቆቃ ጩኸቷን ስትለቀው፤

ወ/ሮ ከሚላ በመቀጠል ምንም ሳያቅማሙ ከፊት ለፊታቸው ያለውን የትርሲትን ጉዳይ የሚከታተለው አቃቤ ህግ ላይ አይናቸውን አፍጥጠው ካስደነገጡት በኋላ ወደ ትርሲት በመዞር አተኩረው ከተመለከቷት በኋላ አትኩሮታቸውን የአበዙን ፋይል ወደ አስቀመጡበት ጠረጴዛ በማዞር አቀርቅረው መነጽራቸውን ከፍ ዝቅ ሲያደርጉ ቆዩና ውሳኔቸውን ለማሰማት ቀና አሉ ።

ፍርድ ቤቱ የወ/ሪት ትርሲትን ጉዳይ በጥልቀት ሲመረምር ቆይቶ ከተከሰሰችባቸው ወንጀሎች በማንኛቸውም ጥፋተኛ ሆና ስላላገኛት በዛሬው እለት ነጻ እንድትወጣ ወስኛለሁ።

ፍርድ ቤቱም ከመቅጽበት የደስታ እምባ ማራጫ ሆነ፤ ውጪው በመፈክሮችም ተጥለቀለቀ።

‹‹ትርሲት እሷ ተሰቃይታ የእውነትን ምንነት አያሳየችን ነው››

‹‹ጀምስ በአስቸኳይ ለፍርድ ይቅረብ››

አቶ ዶን ሽሬዝ የዘመኑ ምርጥ ጠበቃ ናቸው። የመሳሰሉት መፈክሮች የፍርድ ቤቱን ደመቅመቅ አድርገውታል።

አቶ ዶን መፈክሩን ወደ ያዘችው ወጣት በመጠጋት ምስጋናቸውን ካቀረቡላት በኋላ ተከታትለው በመውጣት ከጋዜጠኞች የቀረበላቸውን ጥያቄዎች መልሰው፤ ደጋፊዎቻቸውን አመስግነው፤ ደስታቸውን ለባለቤታቸው ለማብሰር ወደ ሆስፒታል በረሩ ።

የሰሞኑ የሬድዮና የቴሌቭዥን ዜና ሁሉ ስለትርሲት በግፍ መለቃየት ስለሆነ የሚናገረው፤ ብዙ ዜጎችና የህግ አዋቂዎች ስለአሳለፈችው ስቃይ ብቻ ሳይሆን ወደ ፊት ስለምታገኛው ከ1.5 ሚሊዮን እስከ 2 ሚሊዮን የአሜርካን ዶላር ካሳም መነጋገር ጀምረዋል፡፡

**ዘሎርድ ኢዝ ወቺንግ ይልዎታል ይህ ነው ፡፡ እውነትም ከእግዚአብሔር ምን ይሳነውና........**

